# የወጣቶች ትግል ሁሌም አብዮት ለኳሽ ነው

ወርሀ ታህሳስ የወጣት ሰማዕታት ቀን ነው ። እነ ጥላሁን ግዛውና ሌሎች በግፍ የተገደሉበ ትን ወር የሚያስታውሰን ነው። ባለፈውም ሆነ በዘመናዊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ታሪክ ወጣቶች የነበራቸው ሚና ቀላል አልነበረም። ወያኔ ለስልጣን ሲበቃም ወጣቶች ተቃውመው መስዋዕትነትን ከፍለዋል። በ1997ሑም ምርጫ ጊዜ የወያኔን አሳፋሪ ማጭበርብር ተቃውመው ውድ ሕይወታቸውን ያጡት በአብዛኛው ወጣቶች ነበሩ። ለወያኔ ውድቀትም የወጣቶች ትግል መፋፋሙ አስፈላጊና ወሳኝ ነው ።

ሀቀኛ ሀገር ወዳድና ኢትዮጵያዊ ወጣቶች በሀገር አድን ትግሉ ሊሰለፉ እንደተነሱ ሁሉ የፖለቲካ ነጋዴ ወጣቶች ተብዬዎችም የሕዝብን ትግል እያኮላሹ ደፋ ቀና እያሉ ናቸው። ድሮ ወጣት ነበርን የሚሉ ግን ዛሬ የታሪክ አተላ የሆኑ ዶክተር ምሁር ተብዬዎችም ባገኙት መድረክ ሁሉ አንድም ታሪክን ሲበርዙ አሊያም የራሳቸውን ቆሻሻ ታሪክ ለማደስ ብለው ግራ ቀኙን ሲያጠቁ እየታዘብን ነው። ዛሬ በአዲስ አበባ ቤንዚን ጠፍቶ ችግር ከተባ ባሰ አምስተኛውን ቀን ይዟል። ይህ የቀውሱን ደረጃ ጠቋሚ ነው ። ወጣቶች በዩኒቨርሰቲዎ ች ሁሉ ትግል ሲጀምሩ ወያኔ ይህን ትግል የብሄረሰብ/ጎሳ ይዘት በማስያዝ ሊያበላሸው እየጣረ ነው። ለዚህም ነው ወጣቶች ዛሬ የቀድሞዎችን ማስታወስና በአርአያነት መውሰድ መቻል ያለባቸው። የቀድሞ ወጣቶች በሀይማኖት ሆነ ብሄረሰብ መቸም ሳይከፋፈሉ በኢትዮ ጵያዊነት በጋራ ተሰልፈው አድሀሪውን ስርዓት መፋለማቸው ይታወቃል። ለነሱ ዋናው ቀዳሚው ኢትዮጵያ ነበረች። በመሆኑም ለማንም ባዕድ ሀይል ሳይንበረከኩ ሊታገሉ ችለዋል ። ትግል እምነትና ዓላማን ይጠይቃል-- ትግል ወኔንም ፈላጊ ነው። ላመኑበት ዓላማና ለሀገ ር ሕይወትን መስጠት ያስፈልጋል። ሌላ መንገድ ወይም የአቋራጭ መጓዟ ከቶም የለም ። የትግሉ ሻማ ወጣቱ መሆኑን የሚያውቀው ወያኔ በተቻለው መጠን ወጣቱን በራሱ ቋንቋ እንደሚለው ለማምከን ባለው አቅም ሁሉ እየጣረ ነው። ወጣቶች በጋራ ከተነሱ የወያኔ ዕድሜ አጭር መሆኑ ግልፅ ነው። ለዚህም ነው ወያኔ ወጣቶች በጋራ እንዳይታገሉ በየኮሌጅ ፣ ዩኒቨርስቲውና ትምህርት ቤት ሁሉ ትግሉ ፀረ ወያኔ ሳይሆን የርስ በርስ የብሄረሰብ ንትርክና ግጭት ለማድረግ እየሞከረ ያለው። ወጣቶች የታህሳስ ሰማዕትን በማስታወስ በፍፁ ም ኢትዮጵያዊነት ከታገሉ የወያኔ ከፋፋይ ዕቅድ አፈር ይበላል። ከዚያም በላይ ደግሞ ከወያኔና ባዕዳን ጋር ሆነው ሀገርን ሊጎዱና ወያኔን ሊጠቅሙ የሚፈልጉትንም ከሀዲዎች ማሳፈር የሚቻል ነው። ወጣቶች በወያኔ ቅስም ሰባሪ ስምሪትና ዕቅድ ሳይቸነፉ፣ ወያኔ በአዘጋጀው አልባሌና ብልሹ ባሕል ሳይበላሹ ለሀገርና ለወገን ከቆሙ ያለፈውን ትውልድ ቅርስ ወርሰዋል በኩራት ማለት እንችላለን ።

የኢትዮጵያን ትግል ታሪክ ስናጤነው ሁሌም ሕዝብ ለመብቱ በተቻለና በዓቅሙ ሲታገል ባጅቷል:: በአፄው ዘመን የተደረጉ ልዩ ልዩ ትግሎች ለየካቲት 66 ድልዳል ሆነዋል:: ደርግን በመታገል ወጣቶች የከፈሉት መስዋዕትነት ይህ ነው የማይባል ነው:: የቀይ ሽብር አረመኔ ግፍ በአብዛኛው የፈጀው ወጣቱን ነው:: ስንቷ የአለቀሰች እናት፤ ስንት የደም እንባ ያፈሰሰ ቤተሰብ የመንግስቱን ሰው በላነት ያውቃል/ታውቃለች:: ይህ ደነዝ ነፍሰ ገዳይ ታሪኬን ፃፍኩ ብሎ በቅርቡ ባወጣው መፅሃፉ ቀይ ሽብር መካሄዱንም ሲክድ አንበናል:: የዚህ አረመኔ ተባባሪዎች--በተለይም በባዕድ ሀገር ባሉ ድረ ገፆች አውራ ነን ባዮች-- ታሪክ ን ክደው መስዋዕት የሆነውን ወጣት ሊያወግዙ የተነሱት--ዛሬ ወጣቱ በወያኔ ላይ አምርሮ እንዳይነሳ የተቻላቸውን እያደረጉ ነው:: ይህን ነው ወጣቱ ማወቅ መገንዘብ ያለበት:: በአሁኑ ወቅት የወያኔ አገዛዝ በመጨረሻው ቀውስ ላይ ነው:: የተባበረና ጠንከር ያለ ጥቃትና ግፊት ከደረሰበት ውድቀቱ በአጭር ጊዜ ይሆናል:: በዚህ ላይ ምንም ጥርጣሬ ሊኖር አይገባም:: ይህ የሕዝብ አመፅ ከፈነዳ የወያኔ ቁንጮዎችና ቅጥረኛዎች ሁሉ አስጊ ሁኔታ ላይ ይወድቃ ሉ :: የሀገር ወጣቶች ሀገርን አስቀድመው በጋራ በመታገል ለወገን ሊታደጉ የሚችሉ ይሆና ሉ :: ወጣቶች በሰበብ አስባቡ በተለይም ወያኔ ባደረገው ቅስቀሳ የተነሳ እርስ በርሳቸው በሰበ ብ አስባቡ ተከፋፍለው ከተባሉ ተጠቃሚው ወያኔ ይሆናል::

ወጣት ኢትዮጵያውያን ተደራጅተው እንዳይታገሉ ጥቃቱ የሚመጣው ከወያኔ ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ጎራ አካል ነን ከሚሉም አስመሳዮች ነው:: ወጣቶች ሴራውን በማወቅ ለማክሸፍ መታገል አለባቸው:: በሀገር ቤት ወጣቶችን በብሄረሰብና ሀይማኖት ለመከፋፋል ለዓመታት ሲካሄድ የቆየ ዘመቻ አለ :: በዚህ የወያኔ ዘመቻ እነ ኦነግ ዓይነቶቹ ሁሉ ተባባሪዎቹ ናቸው: : ሁሉም ብሄርተኞች ወጣቱ ተከፋፍሎ በአንድነት እንዳይቆም ፈላጊ ናቸው :: ይህም ከእነሱ የሚጠበቅ ነው:: ኢትዮጵያን አምርረው የሚጠሉ ወያኔዎች ወጣቶች ኢትዮጵያ ብለ ው ቢያብሩ የቀብር ደወላቸው ማቃጨሉን ያውቃሉ:: ሰለዚህም ይህ ቀን እንዳይሙጣ ይጥራሉ :: ለዚህም ነው ሕዝብንም በተለይም ወጣቶችንም በብሄረሰብና በሀይማኖት ነጋ ጠባ የሚከፋፍሉት:: ወጣቶች ለትግል አርአያነት ሲጠበቅባቸው ለወያኔ ሰለባ ሆነው በመከፋ ፈልና አልፎም እርስ በርስ በመጋጨት ከተሰማሩ ዋናው ተጠቃሚ ያው ወያኔ ወይም የመለ ስ አገዛዝ ነው:: የክፍፍልና ግንጠላ ዋና ደጋፊ ሆነው መለፈፍ የቀጠሉ ምሁር ተብዬዎችም ራሳቸውን አጋልጠዋል፤ አዋርደዋል:: ተጨማሪ ትችት አስፈላጊ አይሆንም:: ዕይታችንን ወደ ነገ ወስደን ከምን ማድረግ አለብን አንፃር ስናጤነው ግን በተለይም ወጣቶች ከዚህ ቀደ ም እንደታየው ሁሉ በጋራ የአብዮት ለኳሽ ሀይል ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል:: የወያኔ አገዛዝ በውጥረት ገብቶ ሳለ ዝምታ ሳይሆን ተቃውሞን ማስፋፋት አለባቸው:: በሆነው ባልሆ ነው መከፋፈል ሳይሆን አብረው በጋራ በወያኔ ላይ መነሳት አለባቸው:: ይህም ትግልን ጥረ

ትን የሚሻ ተልዕኮ መሆኑየሚያጠያይቅ አይደለም። ወጣቱ ትኩስ የአቢዮት ሀይል በመሆኑ ወጣቱን ውድቅና የማይረባ ለማድረግ እነ ወያኔ ብዙ ሴራ ሸርበው ዛሬ በስራ ሊያውሉ ሩጫ ይዘዋል ። ወጣቱ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኛ፤ የመጠጥና ጫት ተገዢ፤ ሰውነቱን/ቷን ለገበያ አቅ ራቢ እንዲሆን እንድትሆን ፤ ወዘተ ማለትም ወጣቱ ባክኖ እንዲቀሩ ለማድረግ ወያኔ ሲሰራ ቆይቷል። ወያኔ ወጣት ከተበላሸለት የሥልጣን ዕድሜው ይራዘማል። ይህ እንዳለ ሆኖ ማን ም ሀገር ወዳድና ኢሕአፓ ዋና ጠላቱን ወያኔን ረስቶ በሌሎች ላይ የሚረባረብ አልሆነም/ አይደለም። ወጣቱ ኢትዮጵያዊ ሀገርን የማዳን ግዴታውን ለመወጣት መደራጀትና በጋራም መታገል አለበት ። የኢትዮጵያ ወጣት ለሀገሩ ለወገኑ ሲል ለአብዮታዊና ለመሰረታዊ ለወጥ ትግልን በጋራ ማካሄድ ግዴታው ነው ። ከወጣቱ ትውልድ ብዙ ይጠበቃልና